## የሀገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ ቁጥር ሙሲፋ/24/2018

## ያልታጠበ የሀገር ውስጥ ድንጋይ ከሰል ግልፅ ጨረታ

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ለሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ አገልግሎት የሚውል ያልታጠበ የሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል (Raw Local Coal) መጠን 41,500 (አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ) ቶን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በጨረታ የሚሳተፉ ድርጅቶች በዘርፉ የተሰማሩ አምራቾች ወይም አቅራቢ መሆናቸውን የሚገልጽ ህጋዊ የታደሰ ንግድ ፍቃድና የንግድ ምዝገባ ያላቸው፣ አምራች ከሆናችሁ ከክልል መንግሥት የተሰጠ የማዕድን ማምረት ሥራ ፍቃድ ሰርተፍኬት አቅራቢ ከሆኑ የአቅራቢነት ፍቃድ፣ የ2018 ዓ/ም የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የታክስ ከፋይ ተመዝጋቢ የሆኑ የጂኦሎጂካል ሰርቬይ የድንጋይ ከሰል ምርመራ ውጤት እና ይዞታ መግለጫ ማቅረብ የሚችሉ፣ (አስገዳጅ መስፈርት ሲሆኑ አሟልቶ ያላቀረበ ከጨረታው ይሰረዛል) የተጠቀሱትን ማስረጃዎች (ንግድ ምዝገባ፣ የታደሰ ንግድ ፍቃድ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስና የታክስ ከፋይ ምዝገባ ኮፒ) በመያዝ ተጫራቾች የማይመለስ ብር 575.00 ከነቫቱ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን አዲስ አበባ በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት ገርጂ አካባቢ የቀድሞ ኢምፔሪያል ሆቴል መዳረሻ ወሰል ከሚገኘው የፋብሪካው ግዥ መምሪያ ቢሮ እየቀረቡ መግዛት ይችላሉ፡፡ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ብር 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዩን ብር) በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ (Chemical Industry Corporation Mugher Cement Factory) ስም የተዘጋጀ በባንክ በተረጋገጠ ቼክ (C.P.O) ወይም በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ባንክ ጋራንቲ ከቴክኒክ ዶክመንቶቹ ጋር በማያያዝ ይህ ጨረታ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ነሐሴ 26 ቀን 2018 ዓ.ም. ከጥዋቱ 3:30 ሰዓት ድረስ በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ የጨረታ ሰነዳቸውን አዲስ አበባ በሚገኘው በግዥ መምሪያ ቢሮ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

ጨረታው በዕለቱ ነሐሴ 26 ቀን 2018 ዓ.ም. ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት በግዥ መምሪያ ቢሮ ይከፈታል፡፡

ፋብሪካው ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን

ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ

**አዲስ አበባ**